የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፫ አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፪ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.33
ADDIS ABABA 28th August, 2023

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፴፯/፪ሺ፲፭

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……..ገጽ ፲፬ሺ፰፻፸፮

## Content

Regulation No.537/2023

Addis Ababa University establishment Council of Ministers Regulation.........Page 14876

### ደንብ ቁጥር ፭፻፴፯/፪ሺ፲፭

### የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲዎችን ለመደንገግ ባወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፬/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፬(፩) መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፴፯/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩/ **"አዋጅ"** ማለት ስለራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፬/፪ሺ፲፭ ነው፤

### REGULATION NO.537/2023

### Addis Ababa University Establishment Council of Ministers Regulation

The Council of Ministers issued this Regulation in accordance with Article 4(1) of Proclamation No. 1294/2015 issued by the House of Representatives to regulate autonomous universities.

**1. Short title**

These Regulations may be cited as the ''Addis Ababa University establishment Council of Ministers Regulation No. 537/2023''.

**2. Definition**

In this definition, unless the context otherwise requires:

1/ **''Proclamation''** means Proclamation No. 1294/2023;

፪/ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፬/፪ሺ፲፭ አንቀፅ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደአግባብነታቸው ለዚህ ደንብ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

፫/ **"ዩኒቨርሲቲ"** ማለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው፤

፬/ **"ኢንዱስትሪ"** ማለት ማንኛውም በግል፣ በመንግስት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ባለቤትነት ስር የሚገኝ፣ ሴክተር መስሪያ ቤት ወይም በስሩ የሚገኝ ተጠሪ ተቋም ሆኖ ለዩኒቨርሲቲ ስራዎች በትብብርና በጉድኝት መስራት የሚችል የአምራች ዘርፍ ወይም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ወይም ተቋም ነው፤

፭/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል።

**፫. <u>መቋቋም</u>**

፩/ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ዋና አድራሻ በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ወይም ከአገር ውጪ የትምህርት ክፍሎችን፣ የምርምርና የህብረተሰብ ጉድኝት ማዕከላትን ሊያቋቁም ይችላል፤

፫/ የዩኒቨርሲቲው ተግባር እና ሃላፊነት፣ አደረጃጀት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ የአዋጁ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**፬. <u>የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና ሌሎች የህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት</u>**

፩/ የዩኒቨርሲቲው የማስተማሪያ ሆስፒታል የሆነው የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሚደራጀው በዩኒቨርሲቲው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሥር ይሆናል፡፡

2/ The interpretations given in Article 2 of Proclamation No. 1294/2023 shall apply to this Regulation;

3/ **"University"** means Addis Ababa University;

4/ **"Industry"** means a sector office or responsible institution that is owned by a private, government, or non-governmental organization and works collaboratively and cooperatively for the university's work as a manufacturing sector or service provider organization, or institution; and

5/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Establishment</u>**

1/ Addis Ababa University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous university.

2/ The University shall have its main campus in Addis Ababa and may establish other academic units and centers of research and community services in other parts of the country or abroad;

3/ The provisions of the Proclamation shall apply to the University's duties and responsibilities, organization and other relevant matters.

**4. <u>Black Lion Specialized Hospital and Other Medical Service Institution</u>**

1/ The Black Lion Specialized Hospital, the University's teaching hospital, will be organized under the University's College of Health Sciences.

፪/ ሆስፒታሉ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የህክምና አገልግሎት ለሕብረተሰቡ ይሰጣል፤ እንዳስፈላጊነቱ አዳዲስ የህክምና ዘርፎችንና የህክምና መስጫ አማራጮችንም ይከፍታል፡፡

፫/ የነጻ ህክምና ተጠቃሚዎችን መለየት የሚያስችል አሰራርን በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፬/ ዩኒቨርሲቲው የማስተማሪያ ሆስፒታሉን ታሳቢ በማድረግ በመንግስት በብሎክ ግራንት የሚያገኘውን በጀት ድጋፍ መጠን ሙሉ በሙሉ ለማስተማሪያ ሆስፒታሉ ያስተላልፋል፡፡

፭/ በህክምና መስጫ ተቋማቱ የመክፈል አቅም ያላቸው ወይም መደበኛውን የህክምና ቅብብሎሽ ሥርዓት ሳይከተሉ ለሚመጡ ታካሚዎች ተገቢውን ክፍያ በመክፈል አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፮/ ለልምምድ ተማሪዎችን የሚልኩ የግልና የመንግስት ተቋማትን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፡፡

፯/ የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞችና ተማሪዎች የሚያገኙት የህክምና አገልግሎት በዩኒቨርሲቲው የሴኔት ሕግ ይወሰናል፡፡

፰/ ዩኒቨርሲቲው ከጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በተጨማሪ ሌሎች የማስተማሪያ የህክምና ተቋማትን በመክፈት አገልግሎት ላይ ሊያውል ይችላል፡፡

2/ The Hospital provides quality and standard medical services to the community, and opens up new medical fields and treatment options as needed.

3/ It designs and implements a system to identify beneficiaries of free medical treatment;

4/ In consideration of the teaching hospital, the University will fully transfer the amount of government budget assistance obtained through a block grant to the teaching hospital.

5/ It ensures that patients who can afford to pay or who do not follow the normal medical referral system receive services by paying appropriate fees; the details will be determined by the Directive issued by the Board.

6/ It will charge private and government institutions that send students for internships as per the Directive issued by the board.

7/ The medical services available to the employees and students of the University shall be determined by the University's Senate Legislation.

8/ In addition to the Black Lion Specialized Hospital, the University may open other teaching medical institutions.

፭. የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አመራር

፩/ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፦

ሀ) በፕሬዘዳንቱ አቅራቢነት በስራ አመራር ቦርድ የሚሾም ዋና ስራ አስፈፃሚ እና ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚዎች፣

ለ) በፕሬዘዳንቱ አቅራቢነት በስራ አመራር ቦርድ የሚሾም የሆስፒታል የአመራር ቦርድ ይኖረዋል፣

ሐ) አስፈላጊው ሰራተኞች ይኖሩታል።

፪/ የሆስፒታሉ የአመራር ቦርድ አባላትን የስራ ዘመን እና የሚከፈላቸውን የአገልግሎት አበል ጨምሮ ዝርዝር የአመራር ቦርዱ ተግባርና ኃላፊነቶች የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፮. አርማና ማህተም

ዩኒቨርሲቲው በቦርዱ የጸደቀ የራሱ አርማና ማህተም ይኖሩታል፡፡

፯. መመሪያ ስለማውጣት

ቦርዱ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፰. ስለተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲፬/፪ሺ፫ በዚህ ደንብ ተሽሯል፣

፪/ ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣሙ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ልማዶች በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

**5. Management of the Black Lion Specialized Hospital**

1/ Black Lion Specialized Hospital shall have:

a) Chief Executive and Deputy Chief Executives appointed by the Management Board based on the recommendation of the President,

b) Board of Directors of the Hospital appointed by the Management Board based on the recommendation of the President,

c) Will have the necessary staff.

2/ The duties and responsibilities of the Hospital's Management Board members, including the service allowances paid to them, are determined by the directive issued by the university's Management Board.

**6. Logo and Seal**

The University shall have its own logo and seal approved by the Board.

**7. Power to Issue Directive**

The Board may issue Directives to enforce this rule.

**8. Repealed and Non Applicable Laws**

1/ The Addis Ababa University Re-establishment Council of Ministers Regulations No.214/2011 is hereby repealed.

2/ No Regulations, Directives and practices, in so far as inconsistent with the provisions of this Regulation, be applicable on matters covered by this Regulation.

**፱. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**9. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**